صفات عباد الرحمن

የአላህ ባሮች መገለጫዎች



إعداد: الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም ፡ አቡ'ዓብዲልዓዚዝ/ ይሱፍ አህመድ



ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባው ነው። ውዳሴና ሰላምታ ደግሞ በአላህ መልእክተኛ ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን።

ለአላህ አገልጋይ ባሪያ ሆኖ መገኘት ከደረጃዎች ሁሉ ከፍተኛው ደረጃ ነው። ባርነት ነብያቶችን እና የእርሱን ወዳጆች ያወደሰበት መገለጫ ነው። ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ሲል የአምልኮ ባለቤት የሆኑትን ሁሉ ወደራሱ አስጠግቷል።

የልቅና ባለቤት ለሆኑት ምርጥ ባሮቹ የተለያዩና የተባረኩ የሆኑ መገለጫዎችን አላህ ﷾ በተከበረው ቁርኣኑ አውስቷል። እያንዳንዱ ሙስሊም ከዓለማት ጌታ ዘንድ ታላቅን ልቅና ፣ ከፍ ያለን ደረጃ ለመጎናጸፍ በእነዚህ ባህሪያት መገለጽና ባህሪያቱ በሚጠቁሙት መልእክት መስራት ይኖርበታል።

የአማኞች ባህሪያት ከተወሱባቸው የቁረኣን ምዕራፎች መካከል በጣም ግልጹ የፋርቃን ምዕራፍ ነው። በፋርቃን ምዕራፍ ውስጥ ስምንት ኣይነት መገለጫዎችን አውስቷል። የመጀመሪያው መገለጫ "ወዒባዱ ረህማኒ አል'ከዚነ የምሹነ ዓለል አርዲ ሐውነን ..." የሚለው ነው። በዚህ አንቀጽ ውስጥ ፣ ረህማን ያለው የአላህ ﷾ ስም ፣ ባሮቹን በታላቅ ሁኔታ እንደለየ ፣ በእዝነቱ ወደእምነት እንደመራቸው ፣ አላህን በመታዘዝ እና በመልካም ተግባር ወደርሱ በመቃረብ ላይ እንዳነጻቸው ይጠቁማል።

ከዚያም "ወል'ለዚነ" በሚለው የዓረብኛ ስም እያንዳንዱን መገለጫ መቁጠር ጀመረ። ከዚያም እርሱ ባዘጋጀላቸው ታላላቅና የተነባበረ ምንዳ አንቀጾቹን ቋጨ።

ነፍሱ ከእሳት ነጻ እንድትሆን እና መልካም ነገሮችን መጎናጸፍ የፈለገ ሰው በዚህ የተባረከ ቁርኣን ውስጥ የመጡትን የአላህ ባሮች መገለጫዎች በደንብ አስተውሎ እና አውቆ ወደተግባር ለመቀየር እራሱን ማዘጋጀትና መንቀሳቀስ አለበት።

የመጀመሪያው መገለጫ

እርጋታና ክቡር መሆን ፤ ለአላህ እንዲሁም ለባሮቹ መተናነስ

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَعِبَادُ الرَّحْمَنِ الَّذِينَ يَمْشُونَ عَلَى الْأَرْضِ هَوْنًا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ الْجَاهِلُونَ قَالُوا سَلَامًا﴾

"የአል'ረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚሄዱት ፣ ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሯቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው።" *(አል'ፉርቃን፡ 63)*

ከረህማን ባሮች ባህሪና ውብ ከሆኑ መገለጫዎች መካከል ለአላህም ይሁን ለባሮቹ እራስን ማስተናነስ ፤ በርጋታና በአስተውሎት በክብር መጓዝ። በአካሄዳቸውና በአኳኋናቸው ላይ የሚስተዋለው መተናነስ የኢማናቸው ፍሬ ፣ የእርሱው አሻራ ነው።

ኢብን ዓባስ ﵁ "እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚጓዙ" የሚለውን የቁርኣን አንቀጽ "በመልካም በመታዘዝ ፣ ከሀራም ነገሮች በመጠበቅ እና እራሳቸውን በማስተናነስ" በማለት ተርጉመውታል። *(አጥ'ጦቢይ ፊ ተፍሲሪህ፡ 17/491)*

የእርጋታቸውና የመተናነሳቸው መገለጫ በመንገድ ሲጓዙ ጃሒልና ቂል የሆኑ ሰዎች ሲገጥሟቸው ከመጥፎ ነገሮች የጸዳ ትክክለኛና አስተማሪ ንግግር ተናግረው ያልፋሉ።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَإِذَا خَاطَبَهُمُ الْجَاهِلُونَ قَالُوا سَلَامًا﴾

"ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሯቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው።"

"ሰላም የሚሉ ናቸው" ማለት ከሐጢያትና ውድቅ ከሆኑ ንግግሮች ሰላም የሆነ ንግግር ተናግረው የሚያልፉ ናቸው ማለት ነው።

በዚህ ምክንያት የአላህ ባሮች ከሁለት እንቅፋቶች -ከእግር እና ከምላስ እንቅፋቶች- ሰላም ይሆናሉ።

ኢብን አልቀይም ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

((እንቅፋቶች ሁለት በመሆናቸው ምክንያት - የእግርና የምላስ እንቅፋት - በቁርአን አንዱ ከሌላው ጋር ተጣምሮ መጧል።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናገረ፡-

﴿وَعِبَادُ الرَّحْمَنِ الَّذِينَ يَمْشُونَ عَلَى الْأَرْضِ هَوْنًا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ الْجَاهِلُونَ قَالُوا سَلَامًا﴾

"የአልረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚሄዱት ፣ ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሯቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው።" *(አልፉርቃን63)*

አላህ ﷻ ትክክለኛ የሆኑ የረህማን ባሮችን በንግግራቸውም ይሁን በእርምጃቸው ቀጥተኞች እንደሆኑ ገለጻቸው።)) *(አድዳእ ወድደዋእ፡ ገፅ376)*

ጃሂልና ቂል የሆኑ ሰዎች በሚናገሩት በተመሳሳይ ምላሽ አይሰጡም። መጥፎ ሲናገሯቸው ከዚህ አደጋ ሰላም የሚሆኑበትን ንግግር ተናግረው ገለል ይላሉ። ባጠቃላይ መጥፎውን በመልካም ይከላከላሉ።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلَا تَسْتَوِي الْحَسَنَةُ وَلَا السَّيِّئَةُ ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا الَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُ عَدَاوَةٌ كَأَنَّهُ وَلِيٌّ حَمِيمٌ﴾وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا الَّذِينَ صَبَرُوا وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا ذُو حَظٍّ عَظِيمٍ﴾

"መልካሚቱና ክፉይቱም (ጸባይ) አይስተካከሉም። ከዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ጸባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር።ያን ጊዜ ያ ባንተና በእርሱ መካከል ጠብ

ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይሆንልሀል። (ይህችንም ጠባይ) እነዚያ የታገሱት እንጅ ሌላው አያገኟትም። የትልቅም ዕድል ባለቤት እንጅ ሚንም አይገጠሚትም።" (ፉሲለት፡ 34-35)

ሰዎች በስነ-ምግባርና ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አላቸው። ታዲያ ሙስሊሞች በዲን ውበትም ይሁን በስነ-ምግባር ጥሩነት ከዚህ በፊት አላህ ባወሳው አይነት ሊገለጹ ይገባል። መጥፎውን በመልካም መመለስ ፣ ስነ-ምግባራቸው ምንም ይሁን ምን ለአላህ ባሮች እራሳቸውን ማስተናነስ ይኖርባቸዋል።

ከዚህ ሁሉ በፊት በማንኛውም ነገር በአላህ መታገዝ ይገባል። ለመልካሚ ስነ-ምግባር አላህ እንዲመራው ፣ ከመጥፎዋ ደግሞ እንዲያርቀው ዱዓ ማድረግ አለበት።

ረሡል ﷺ በሶላት መክፈቻ ላይ የሚከተለውን ዱዓ ያደርጉ ነበር፡-

"اهدني لأحسن الأخلاق، لا يهدني لأحسنها إلا إنت، واصرف عني سيئها، لا يصرف سيئها إلا أنت"

"ከመልካም ስነ-ምግባሯ ምራኝ ፤ ከመልካሚ የሚመራ የለም አንተ ብትሆን አንጅ ፤ መጥፎዋን ከአኔ ላይ አርቅልኝ ፤ መጥፎዋን የሚያርቅ የለም አንተ ብትሆን አንጅ።"
(ሙስሊም፡ 771)

ረሡል ﷺ ከቤቱ ለሚወጣ ሰው የሚከተለውን ዱዓ እንዲያደርግ አቅጣጫ ሰጠውታል፡-

"اللهم أعوذ بك أن أضل أو أضل ، أو أزل أو أزل ، أو أظلم أو أظلم ، أو أجهل أو يجهل علي"

"አላህ ሆይ በአራሴም በሌላም ከመጥመም ፣ በራሴም ይሁን በሌላ ከወንጀል ላይ ከመውደቅ ፣ ሌላን ከመበደልና በሌላ ሰው ከመበደል፣ራሴም የማሕይማን ስራ ከመስራት

በኬላም አላፊ አንዳይሰራብኝ በአንተ አጠበቃለሁ።" *(አቡዳውድ፡ 5094, ቲርሚዚይ፡ 3427, ኑሳኢይ፡ 5501, አልባኒ ሐዲሱን ሶሂህ ብለውታል "ሶሂህ አት' ቲርሚዚይ፡ 5094")*

ይህ ፣ ባሪያው በራሱም ላይ ይሁን በሌሎች ፣ የማሕይምነት ስራ እንዳይሰራ እንዲሁም እንዳይስሰራበት የሚጠብቅና ከጸያፍ ስነ-ምግባር ሰላም የሚያደርግ የተባረከ ዱዓ ነው።

ሁለተኛው መገለጫ

ሶላትን - በተለይም የሌሊት ሶላቶችን - ተጠባብቆ መስገድ

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ يَبِيتُونَ لِرَبِّهِمْ سُجَّدًا وَقِيَامًا﴾

"እነዚያም ከጌታቸው በግንባራቸው ተደፊዎችና ቋሚዎች ሆነው የሚያድሩት ናቸው።" (አል'ፉርቃን፡ 64)

ከአላህ ባሮች መገለጫዎች መካከል ከአካል ተግባራት ትልቁ የሆነውን ፈርድም ይሁን ሱና ሶላቶች ተጠባብቆ መስገድ ነው። በተለይም የሌሊትን ሶላት። የሌሊት ሶላትን ተጠባብቆ መስገድን በተመለከተ በርካታ ሐዲሶች መጠዋል።

ሌሊት ተነስቶ ሶላት መስገድን በተመለከተ ከመጡ መረጃዎች መካከል የሚከተለው የረሡል ﷺ ሐዲስ ይገኝበታል፡-

"أفضل الصلاة بعد الفريضة : صلاة الليل"

"ከፈርዱ በኋላ ከሶላቶች ሁሉ በላጩ የሌሊት ሶላት ነው።" (ሙስሊም፡ 1163)

አሁንም ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"عليكم بقيام الليل ، فإنه دأب الصالحين قبلكم ، وهو قربة إلى ربكم ، ومكفرة للسيئات ، ومنهاة للإثم"

"አደራ ሌሊት ሰዓት ላይ መቆምን ፣ (ሌሊት መቆም) ከናንተ በፊት የነበሩት ሷሊሆች ልማድ ነው ፣ ወደጌታችሁም መቃረቢያ ፣ ሐጢያትን መሰረዣ ፣ ከወንጀልም ከልካይ ነው።" (አህመድ፡ 24945, ቲርሚዚይ፡ 3549, ሐዲሱን አልባኒ ሐሰን ብለውታል "መሸካቱ አል'መሷቢህ፡ 1227")

የሌሊት ሶላት መቆሚያ ወቅት ፡-

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ሌሊት ሙሉ ሲሰግዱ አድረዋል ፣ መጀመሪያ ሌሊት ሰግደዋል ፣ ከሌሊት መካከል ላይ ሰግደዋል ፣ ከሌሊት መጨረሻም ሰግደዋል። ከዚያም ከሌሊት ሰዓታት ሁሉ በላጭ በሆነው የሌሊት መጨረሻ ከሆነው የሱሁር ወቅት ላይ በቋሚነት በመቆም መጽናታቸው ይታወቃል። ይህ ወቅት ጌታችን አላህ ﷻ ወደቅርቢቱ ሰማይ የሚወርድበት ወቅት በመሆኑ ከሌሊት ወቅቶች ሁሉ በላጩ ነው።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"ينزل ربنا تبارك وتعالى كل ليلة إلى السماء الدنيا حين يبقى ثلث الليل الآخر ، يقول : من يدعوني فأستجيب له ، من يسألني فأعطيه ، من يستغفرني فأغفرله"

"የመጨረሻው የኼኺቱ አንዱ ሶስተኛው ሲቀር በየኼኺቱ ፣ ጌታችን ወደቅርቢቱ ሰማይ ይወርዳል። "ማን ነው የሚለምነኝ ለእርሱ የምቀበለው ፣ ማን ነው የሚጠይቀኝ የምሰጠው ፣ ማን ነው ይቅርታን የሚጠይቀኝ ምህረት የማደርግለት ይላል።" *(ቡኻሪ፡ 1145, ሙስሊም፡ 758)*

ማንኛውም ነፍሱን መካሪ የሆነ የአላህ ባሪያ ታላቅን ደረጃ ለማግኘት ፣ ከሌሊት ሶላት ቀላል የሆኑ ሁለት ረከዓዎችን እንኳ ሊሰግድ ይገባዋል።

በአጠቃላይ የአላህ ባሮች በሌሊት ሰዓት መቆማቸውም ፣ መጎንበሳቸውም ፣ ፍርሃታቸውም ፣ መተናነሳቸውም ፣ ከአላህ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነትም ይሁን የአምልኮ ሁኔታቸው ይህን ይመስላል።

የአላህ ባሮች በሌሊት ሰዓት - አላህ በእነርሱ ላይ ግዴታ ባላደረገው - ዒባዳ ላይ ያላቸው ባህሪ ይህን ከመሰለ ከሸሐደተይን (ከሁለቱ የምስክርነት ቃሎች) ቀጥሎ ፣

አላህ የዲኑ ማዕዘን ባደረገው አምስት የግዴታ ወቅት ሶላት ላይ እንዴት ሊሆኑ ነው? !

በእርሷ ላይ ብርቱ ጉጉት ኖሯቸው ወቅት ጠብቀው መስገዳቸው ምንም የሚያጠራጥር አይደለም።

ሰባተኛው መገለጫ

ከእሳት ቅጣት መፍራታቸውና መጨነቃቸው

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا اصْرِفْ عَنَّا عَذَابَ جَهَنَّمَ إِنَّ عَذَابَهَا كَانَ غَرَامًا۝إِنَّهَا سَاءَتْ مُسْتَقَرًّا وَمُقَامًا﴾

"እነዚያም ከጌታቸው በግንባራቸው ተደፊዎች ቋሚዎች ሆነው የሚያድሩት ናቸው። እነዚያም "ጌታችን ሆይ! የገሀነምን ቅጣት በእኛ ላይ መልስልን ቅጣቷ የሚይዘቅ ነውና" የሚሉት ናቸው። እርሷ መርጊያና መቀመጫ በመሆን ከፋች! (ይላሉ)፡ (ፉርቃን65-66)

የአላህ ባሮች ስራቸውን እንዲሁም አምልኮታቸውን ከማሳመራቸው ጋር ከአላህ ቅጣትንና ቁጣን ይፈራሉ ፣ ይደነግጣሉ። ይህ ደግሞ የተሟላ ስነ-ምግባር ያላቸው መእሚኖች ባህሪ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ يُؤْتُونَ مَا آتَوا وَّقُلُوبُهُمْ وَجِلَةٌ أَنَّهُمْ إِلَى رَبِّهِمْ رَاجِعُونَ﴾

"እነዚያም የሚሰጡትን ነገር እነርሱ ወደ ጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡት።" (አል'መእሚኑን፡ 60)

የታዘዙትን ፈጽመው ሲያበቁ ስራችን ተቀባይነት ያጣል ፣ ከአላህ የሆነ ቅጣት ይደርስብናል ብለው የሚፈሩና የሚሰጉ ናቸው።

ከዚህ በፊት ስላሳለፍነው የቁርአን አንቀጽ ትርጉም ዓኢሻ ﵂ "እነዚህ ሰዎች አስካሪ መጠጥ የሚጠጡ ፣የሚሰርቁ ሰዎች ናቸው?" በማለት ረሡልን ﷺ ጠየቀች።

የአላህ መልእክተኛም ﷺ የሚከተለውን መልስ ሰጧት፡-

"لا يا بنت الصديق ، ولكنهم الذين يصومون ويصلون ويتصدقون ، وهم يخافون أن لا تقبل منهم"

"የ (አቡበክር) ሲድቅ ልጅ ሆይ! (ነገሩ አንች አንደምትይው) አይደለም ፤ ነገር ግን አነዚያ ስራችን ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም ብለው የሚጸሙ ፣ የሚሰግዱ አና ሶደቃ የሚሰጡ ናቸው።" (አህመድ፡ 24641, ቲርሚዚይ፡ 3175, ኢብኑ ማጀህ፡ 4198, ሑዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል "ሶሂህ ቲርሚዚይ፡ 3175)

ሐሰን አልበስርይ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"المؤمن جمع إحسانا وشفقة، والمنافق جمع إساءة وأمنا،

"ሙእሚን በጎ ስራን እና ፍርሐትን በአንድ ላይ ሰብስቦ ይዟል ፣ ሙናፊቅ ደግሞ ክፉ ስራን እና (ከቅጣት) መተማመንን በአንድ ላይ ሰብስቦ ይዟል።"

ከዚያም የሚከተለውን ቁርኣናዊ አንቀጽ አነበቡ፡-

﴿إِنَّ الَّذِينَ هُم مِّنْ خَشْيَةِ رَبِّهِم مُّشْفِقُونَ﴾

"እነዚያ እነርሱ ጌታቸውን በመፍራት የተነሳ ተጨናቂዎች የሆኑት።" (አል ሙእሚኑን፡ 57) (አጥ'ጦበረይ ፊ ተፍሲሪህ፡ 17/68)

ሙናፊቅ - አላህ ይጠብቀንና - በሙእሚን ተቃራኒ ስራውን ያከፋል ፣ ይህ ከመሆኑ ጋር ምንም ሳይፈራ እኔን ምንም አይነት ቅጣት አይነካኝም ብሎ ይተማመናል። ሙእሚን ፣ ልክ የአላህን እዝነት መፈለጉ መልካም ስራን ለመስራት ፣ ከአላህ ትሩፋትን ለማግኘትና ወደአላህ ለመቃረብ እንደሚያግዘው ሁሉ ፣ ከአላህ ቅጣትን መፍራቱ ደግሞ ወንጀልን ከወዲሁ እንዲርቅ እና እንዲጠነቀቅ ያደርገዋል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿أُولَئِكَ الَّذِينَ يَدْعُونَ يَبْتَغُونَ إِلَى رَبِّهِمُ الْوَسِيلَةَ أَيُّهُمْ أَقْرَبُ وَيَرْجُونَ رَحْمَتَهُ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُ إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ كَانَ مَحْذُورًا﴾

"እነዚያ እነርሱ የሚግገዟቸው (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደጌታቸው መቃረቢያን (ስራ) ይፈልጋሉ። እዝነቱንም ይከጅላሉ። ቅጣቱንም ይፈራሉ። የጌታህ ቅጣት የሚፈራ ነውና።" (አል'ኢስራእ፡ 57)

ከዚህ ቀደም ያሳለፍነው የአላህ ባሮች ዱዓ ፣ እሳት ለመግባት ምክንያት የሚሆኑ ስራዎችን በዚህ በዱንያ ሒዎት እንዲያርቅላቸው ዱዓ ማድረጋቸውን ያካትታል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا اصْرِفْ عَنَّا عَذَابَ جَهَنَّمَ إِنَّ عَذَابَهَا كَانَ غَرَامًا﴾

"እነዚያም "ጌታችን ሆይ! የገሀነምን ቅጣት በእኛ ላይ መልስልን ቅጣቷ የሚይዘቅ ነውና" የሚሉት ናቸው።" (አል'ፉርቃን ፡ 65)

ረሡል ﷺ ለሙእሚኖች እናት የሚከተለውን ዱዓ አስተምረዋታል፡-

"اللهم إني أسألك الجنة ، وما قرب إليها من قول أو عمل ، وأعوذ بك من النار ، وما قرب إليها من قول أو عمل"

"አላህ ሆይ! አኔ ጀነትን አጠይቅሃለሁ ፤ ከንግግርም ወይም ከተግባር ወደርሷ የሚያቀርብንም አጠይቅሃለሁ። ከእሳት በአንተ አጠበቃለሁ ፤ ከንግግርም ወይም ከተግባር ወደርሷ የሚያቀርብን በአንተ አጠበቃለሁ።" (አህመድ፡ 25019, ኢብኑ ማጀህ፡ 3846, አልባኒ ሐዲሱን ሶሂህ ብለውታል "አስ'ሲልሲቱ አስ'ሶሂህ፡ 1542)

የረህማን ባሮች የጀሀነም (ቅጣቷ) ብርቱና ሁልጊዜ የማይለቅ በመሆኑ የሚከተለውን

ዱዓ ያደርጋሉ፡-

﴿وَالَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا اصْرِفْ عَنَّا عَذَابَ جَهَنَّمَ إِنَّ عَذَابَهَا كَانَ غَرَامًا۝إِنَّهَا سَاءَتْ مُسْتَقَرًّا وَمُقَامًا﴾

"የገሀነምን ቅጣት በእኛ ላይ መልስልን ቅጣቷ የሚይዘቅ ነውና" የሚሉት ናቸው። እርሷ መርጊያና መቀመጫ በመሆን ከፋች! (ይላሉ)። *(አል'ፉርቃን65-66)*

አራተኛው መገለጫ

በማባከን እና በንፉግነት መካከል ላይ ሆነው ገንዘባቸውን የሚለግሱ ናቸው

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ إِذَا أَنفَقُوا لَمْ يُسْرِفُوا وَلَمْ يَقْتُرُوا وَكَانَ بَيْنَ ذَٰلِكَ قَوَامًا﴾

"እነዚያም በሐገሱ ጊዜ የሚያባክኑ የሚይቀጥቡትም ናቸው። በዚህም መካከል (ልግስናቸው) ትክክለኛ የሆነ ነው።" (አል'ፉርቃን፡ 67)

የአላህ ባሮች ፣ አላህ ﷻ ከሰጣቸው ጸጋ ለወደፊት እንደሚጠይቃቸው ስለተገነዘቡ ገንዘባቸውን በማባከን እና በመቆጠብ መካከል ሆነው የሚለግሱ ናቸው።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"لا تزول قدما عبد يوم القيامة حتى يسأل عن عمره فيم أفناه، وعن علمه فيم فعل، وعن ماله من أين اكتسبه، وفيم أنفقه، وعن جسمه فيم أبلاه"

"አድሚው በምን እንደሳለፈው ፣ እውቀቱን ምን እንደሰራበት ፣ ገንዘቡን ከምን ሰርቶ እንደመጣው ፣ ከምን ወጭ እንዳዋለው ፣ ሰውነቱን በምን እንደጨረሰው ሳይጠየቅ የባሪያው ሁለቱ ጫማዎች (ከቆመበት) ፈቀቅ አይሉም።" (ቲርሚዚይ፡ 2417, አድ'ዳሪሚይ፡ 554, ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል "አስ'ሲልሲቱ ሶሂህ፡ 946)

የአላህ ባሮች በግዴታነትም ይሁን በሱና መልኩ በሚለግሱ ጊዜ የሚቆጥቡም ፣ አላህ ከፈቀደላቸው በላይ ድንበር አልፈው የሚያባክኑ አይደሉም። በማይቀሩና ወሳኝ በሆኑ ነገሮች ላይ ወጭ ለማውጣት ደግሞ ፈጣኖች ናቸው። ለምሳሌ፡- ለሐዎታቸው የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ጉዳዮች ፣ አኼራቸውን ለማስተካከል የሚያግዙ ስንቆች ላይ ወጭ ለማውጣት ወደኋላ የሚሉ አይደሉም።

በሙስሊም ላይ ያለውም ግዴታ ይህ ነው። የአላህ ባሮች በዲንም ይሁን በዱንያ ማንኛውም ጉዳዮች ወሰንም አያልፉም ፣ የዘቀጠ አመለካከትም የላቸው።

ኢብን ፈሩኽ ከቀታዳ ፣ ቀታዳ ደግሞ ከሙጥሪፍ ብን ዓብዲላህ ﵀ በመያዝ ሙጥሪፍ የሚከተለውን ንግግር ተናግሯል፡-

"خير هذه الأمور أوساطها، والحسنة بين السيئتين"

"ከነገሮች ሁሉ መልካሙ መካከለኛው ነው። መልካም በሁለት ክፉዎች መካከል ነው።"

"በሁለት ክፉዎች መካከል ያለው መልካም ምንድነው?" በማለት ሙጥሪፍ ቀታዳን ጠየቀው። ቀታዳም "እነዚያም በኪሳቸው ጊዜ የሚያባክኑ የሚይቆጥቡትም ናቸው።" የሚለውን የቁርኣን አንቀጽ አነበበ። *(አጥ' ጦበሪይ ፊ ተፍሲሪሀ 17/500)*

አምስተኛው መገለጫ

ከከባድ ወንጀል እና ከታላላቅ ሐጢያቶች መራቃቸው

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ لَا يَدْعُونَ مَعَ اللَّهِ إِلَٰهًا آخَرَ وَلَا يَقْتُلُونَ النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ وَلَا يَزْنُونَ﴾

"እነዚያም ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የሚይገዙት ፣ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ የሚይገድሉት ፣ የሚያመነዝሩትም ናቸው።" *(አል'ፉርቃን፡ 68)*

አላህን ከሚፈሩ ባሮች መገለጫዎች መካከል አንዱ ከባድ ወንጀሎችና ሐጢያቶችን መራቅ ነው። አላህ በዚህ ቁርኣናዊ አንቀጽ ሶስት ከባድ ወንጀሎችን በተለየ ሁኔታ አውስቷል።

1. በአላህ ማጋራት
2. ጥብቅ የሆነችን ነፍስ መግደል
3. ዝሙት መፈጸም ናቸው።

ማጋራት አላህ በባሮች ላይ ክልክል ካደረገባቸው ነገሮች ትልቁና ዋነኛው ነው። አንድ ሰው ይህን ወንጀል ፈጽሞ ቢሞት አላህ እንደማይምረው በሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ አስረግጦ ተናግሯል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِنَّ اللّهَ لاَ يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَلِكَ لِمَن يَشَاء وَمَن يُشْرِكْ بِاللّهِ فَقَدِ افْتَرَى إِثْمًا عَظِيمًا﴾

"አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ሀጢያት) ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ሃጢአት በእርግጥ ቀጠፈ።" *(አን'ኒሳእ፡ 48)*

አንድ ባሪያ ዱዓ ፣ ኢስቲጋሳ (ተማጽኖ) ፣ ነዝር (ስለት) ፣ እርድ እና ከመሳሰሉ አምልኮዎች አንዱን አሳልፎ ለሌላ አካል ከሰጠ ይቅር የማይባል ወንጀል ፈጽሟል ፤ በአላህም አጋርቷል።

ንጹህ የሆነችን ነፍስ መግደል ደግሞ አስቀያሚ ከሆኑ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው። አንዲት ነፍስ ያላግባብ ከተገደለች የእርሷ ሐቅ በሶስት ሰዎች ላይ ይንጠለጠላል። ያለአግባብ በግፍ በገደለው ፣ በተገዳዮ እና በተገዳይ ቤተሰቦች ይንጠለጠላል።

ይህን አስመልክቶ ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"لزوال الدنيا أهون على الله من قتل مؤمن بغير حق"

"ያለአግባብ ሙአሚንን ከመግደል ዱንያ (በአጠቃላይ) መወገዷ ከአላህ ዘንድ የቀለለ ነው።" (ኢብኑ ማጀህ፡ 2619, ሐዲሱን አልባኒ ፊሶሂህ ብለውታል "ፊሶሂህ አልጃሚዕ፡ 5078)

ዝሙት ፣ ልቦናን የሚያሳምምና የሚያበላሽ ፣ አስጸያፊና ከባድ ከሆኑ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው። ዝሙት በማህበረሰብ ፣ በግለሰብ ኢማን ፣ በአካል ፣ በነፍስ እና በአጠቃላይ በማህበራዊ ህይዎት ላይ ከባድ ጉዳትና ቀውስ ይፈጥራል።

ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"إذا زنى الرجل خرج منه الإيمان وكان عليه كالظلة، فإذا انقطع رجع إليه الإيمان"

"አንድ ሰው ዝሙት የሰራ ጊዜ ከአርሱ ላይ ልክ አንደጥላ ሆኖ ኢማኑ ከፍ ብሎ ይቆያል ፣ ከዚህ ተግባሩ ካቋረጠ ደግሞ ኢማኑ ወደርሱ ይመለሳል።" (አቡዳውድ፡ 4690, ቲርሚዚይ፡ 2625, ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል "አስ'ሲልሲለቱ ሶሂህ፡ 509)

አላህም ይሁን ረሡል ﷺ ወደጸያፍ ነገሮች የሚያቃርቡ ነገሮችን ከልክለዋል። አንዲት ሴትና ባዕድ የሆነ ወንድ በአንድ ክፍል አብረው መቀመጥ እንደሌለባቸው

አስጠንቅቀዋል። ለመሀረሟ (ማግባት የማትችላቸው ወንዶች) ካልሆነ በቀር ከአካሏ መገለጥ እንደሌለባት አበክረው ተናግረዋል። ሽቶ ተረጭታ በአደባባይ መውጣት እንደሌለባት ፤ ወንዶችም ይሁን ሴቶች ባእድ ሲመለከቱ አይናቸውን መመለስ እንዳለባቸው ፤ በአጠቃላይ ህብረተሰብን ለመጠበቅ ሲባል ከነዚህ የከበዱ አደገኛ ወንጀሎች ላይ ሙስሊሞች እንዳይወድቁ የሚከለክሉ አምላካዊ ህግጋቶችን ደንግገዋል። አላህ ﷻ ባሮቹ ከነዚህ ሶስት ከባድ ከሆኑ ወንጀሎች እንዲርቁ ካስታወሰ በኋላ እነዚህን ወንጀሎች የፈጸመ የተነባበረና በጀሐነም ውስጥ ብርቱ የሆነ ቅጣት እንደሚገጥመው አያይዞ ተናግሯል፡-

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ يَلْقَ أَثَامًا ۝ يُضَاعَفْ لَهُ الْعَذَابُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ وَيَخْلُدْ فِيهِ مُهَانًا﴾

"ይህንንም የሚሰራ ሰው ቅጣትን ያገኛል። በትንሳኤ ቀን ቅጣቱ ከእርሱ ይደራረባል። በእርሱም ውስጥ የተዋረደ ሆኖ ይኖራል።" *(አል'ፉርቃን፡ 68-69)*

ከዚህ ብርቱ ዛቻ የሚያመልጠው እንዲሁም የአላህን ይቅርታ የሚጎናጸፈው ፣ ደረጃው ከፍ ብሎ ሐጢያቱ በመልካም የሚቀየርለት ፣ ከነበረበት ወንጀል ተጸጽቶ ወደጌታው የተመለሰ ፣ ወደርሱ የሚያቃርብን መልካም ስራን ያበዛና ለጽድቅ ተግባራት የተሸቀዳደመ ብቻ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِلَّا مَن تَابَ وَآمَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَالِحًا فَأُولَٰئِكَ يُبَدِّلُ اللَّهُ سَيِّئَاتِهِمْ حَسَنَاتٍ وَكَانَ اللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا﴾

"ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ መልካምንም ስራ የሰራ ሰው ብቻ ሲቀር። እነዚያም አላህ መጥፎ ስራዎቻቸውን በመልካም ስራዎች ይለውጣል። አላህም እጅግ መሃሪ አዛኝ ነው።" *(አል'ፉርቃን ፡ 70)*

ስድስተኛው መገለጫ

ጸያፍ ተግባራት ከሚፈጸምባቸው ቦታዎች መራቅ

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ لَا يَشْهَدُونَ الزُّورَ وَإِذَا مَرُّوا بِاللَّغْوِ مَرُّوا كِرَامًا﴾

"እነዚያም እብከትን የሚይመሰክሩ ፤ በሙድቅ ቃልም (ተናጋሪ አጠገብ) ባለፉ ጊዜ የከበሩ ሆነው የሚያልፉት ናቸው።" *(አል'ፉርቃን፡ 72)*

ከአላህ ባሮች መልካም ስነ-ምግባር ፣ ውብ ከሆነው መገለጫዎቻቸው መካከል በመጥፎ ነገሮች ፣ በውሸት ፣ በሀሬም እና በውድቅ ቃላቶች የተከበበ መድረክ ላይ ከመገኘት ይርቃሉ።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ لَا يَشْهَدُونَ الزُّورَ﴾

"እነዚያም እብከትን የሚይመሰክሩ"

ይህ ቁርኣናዊ አንቀጽ የአላህ ባሮች ውሸት ፣ ቅጥፈት ከሚነገርበት ቦታ አይቀመጡም የሚል መልእክት አለው። ከእንዲህ አይነት ሰዎችም ጋር ጓደኛ አይሆኑም።

ባለፈው አንቀጽ ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦች፡-

1. መሰረቱን ወንጀልና ሐጢያት ያደረገ ስብስብ፡ ሀሜት ፣ ነገር ማዋሰድ ፣ ማላገጥ ፣ ማሾፍ ፣ ውሸት ፣ ዘፈን ፣ ጸያፍ የሆኑ ነገሮችን መመልከትና የመሳሰሉት ናቸው።
2. ጠማማ አመለካከቶች የሚሰራጩባቸው መድረኮች፡ ብልሹ አካሄዶች ፣ የመጥፎ እና የጥመት ተጣሪዎች የሚፈጥሯው ቢድዓዎች የሚሰራጩበት መድረክ ነው።

3. የሙሽሪክ በዓል የሚከበሩባቸው ቦታዎች ፡

ከላይ በዘረዘርናቸው ሶስት ቦታዎች ሁሉ ማንኛውም ሙስሊም መገኘቱ ሀራም ነው።

አሁን ያሳለፍነው ትርጉም ሁሉ በአንቀጹ ውስጥ ይካተታል። ለዚህ ነው በአንቀጹ ውስጥ የሚገኘውን "ዙር" የሚለውን የዓረብኛ ቃል ቀደምት ሰለፎች በተለያየ አተረጓጎም የተረጎሙት።

ሀፊዝ ብን ሐጀር አጥጦበሪ ﵀ የሰለፎችን ንግግር ካቀረበ በኋላ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

((የዚህን ቃል ትርጉም በተመለከተ በላጩ የሚከተለው ነው፡ ቅጥፈት ባለበት ቦታ ሁሉ የማይገኙ ፣ ሽርክም ይሁን ፣ ዘፈን ፣ ውሸትም ይሁን ፣ ሌላ። "ዙር" የሚለው ሰም ያቀፈው ሁሉ በዚህ ውስጥ ይካተታል። ምክንያቱም አላህ መገለጫቸውን ጥቅል አድርጎ "እብለትን የማይመሰክሩ (የማይጣዱ) በማለት ገልጿቸዋል")) (ጀሚው አል'ቢያን፡ 17/523)

የአላህ ባሮች እንኳን ከእነርሱ ላይ ሊከሰት ቀርቶ በማንኛውም መልኩ ውሸት በሚዋሸበት ቦታ ሁሉ አይገኙም።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የአላህን ባሮችን እንደሚከተለው ይገልጻቸዋል፡-

﴿وَإِذَا مَرُّوا بِاللَّغْوِ مَرُّوا كِرَامًا﴾

"ባከፉ ጊዜ የከበሩ ሆነው የሚያልፉት ናቸው።"

የአላህ ባሮች በወንጀል የተዘፈቁ አይደሉም። ወንጀልንም አይቀርቡም። ነገር ግን ድንገት የወንጀል ቦታ ቢያጋጥማቸው እራሳቸውን በማግለል ፣ በቦታዋ ሳይደበለቁና ሳይቀመጡ የተከበሩ ሆነው ያልፋሉ።

ሰባተኛው መገለጫ

ለአላህ ንግግር ክብር ይሰጣሉ ፣ በውስጡ ያለውን መልእክትም ይቀበላሉ

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ إِذَا ذُكِّرُوا بِآيَاتِ رَبِّهِمْ لَمْ يَخِرُّوا عَلَيْهَا صُمًّا وَعُمْيَانًا﴾

“እነዚያም በጌታቸው አንቀጾች በተገሰጹ ጊዜ (የተረዱ ተቀባዮች ሆነው እንጂ) ደንቆሮዎችና እውሮች ሆነው በእርሷ ላይ የሚይደፉት ናቸው።” *(አልፉርቃን፡ 73)*

የአላህ ንግግር በባሮቹ ልቦና ውስጥ ታላቅ ቦታ የሚሰጠው እንጅ በእምቢተኝነትና በአመጽ የሚቃወሙት አይደለም። ይልቁንም ያልቁታል ፣ ያከብሩታል ፣ በጥሩ ሁኔታ ለመጠቀም ጀሮ ሰጠው ያደምጡታል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿لَمْ يَخِرُّوا عَلَيْهَا صُمًّا وَعُمْيَانًا﴾

“ደንቆሮዎችና እውሮች ሆነው በእርሷ ላይ የሚይደፉት ናቸው።”

የጌታቸውን ቃል ባዳመጡ ጊዜ ልክ በምክሩ እንደማይጠቀም ደንቆሮ ፣ ህቅን እንደማይመለከት እውር ሆነው አያልፉም። ይልቁንም በደንብ ያዳምጣሉ ፣ በምክሩ ይጠቀማሉ ፣ በህግጋቱ ይሰራሉ ፣ በውስጥ ባለው ብርሃን ይመራሉ።

ቀታዳ ብን ደዓመተ በዚህ አንቀጽ ዙሪያ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

“ከሐቅ ደንቆሮ የማይሆኑ ፣ በእርሱ ዙሪያ ያልታወሩ ፣ እነርሱ ናቸው ስለአላህ የተገነዘቡ ፣ ከአላህ ኪታብ በሰሙት የሚጠቀሙ።” *(ኢብኑ አቢ ሃቲም፡ ተፍሲሪህ፡8/2740)*

በአላህ አንቀጾች ከመመራት የሚከሩትን ትዕቢተኞች ፣ በሀጢያታቸው ዘውታሪዎችን አላህ አውግዟል ፣ በጀሀነም ቅጣትም ዝቶባቸዋል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَإِذَا قِيلَ لَهُ اتَّقِ اللَّهَ أَخَذَتْهُ الْعِزَّةُ بِالْإِثْمِ﴾

“ከእርሱ “አላህን ፍራ” በተባለም ጊዜ ፤ ትእቢቱ በሀጢአት (ስራ) ላይ ትገፋፋዋለች።” *(አል’በቀራህ፡ 206)*

ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

"إن أبغض الكلام إلى الله أن يقول الرجل للرجل: اتق الله، فيقول: عليك نفسك"

“ከአላህ ዘንድ ከንግግሩ ሁሉ በጣም የሚያስቆጣው ፣ አንድ ሰው አላህን ፍራ በማለት ለሌላው ሲነግረው። የተነገረው ሰው መልሶ በነፍስህ ላይ አደራ!” የሚለው ነው።”

(አስ’ሲልሲቱ አስ’ሶሂህ፡ 2939)

ስምንተኛው መገለጫ

በዱዓ ላይ ትኩረት መስጠታቸው ፣ ለአላህ መተናነሳቸው

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَالَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا هَبْ لَنَا مِنْ أَزْوَاجِنَا وَذُرِّيَّاتِنَا قُرَّةَ أَعْيُنٍ وَاجْعَلْنَا لِلْمُتَّقِينَ إِمَامًا﴾

"እነዚያም "ጌታችን ሆይ! ከሚስቶቻችንና ከዘሮቻችን ከዓይኖች መርጊያን ከእኛ ስጠን። አላህን ከሚፈሩትም መሪ አድርገን" የሚሉት ናቸው።" *(ኸል'ፉርቃን፡ 74)*

ከአላህ ባሮች የተሟላ ባህሪ መካከል በዱዓ ላይ ያላቸው ትኩረት ነው። ወደአላህ ዘወትር ይጠጋሉ። ፊታቸውን ወደርሱ ያዞራሉ። የዲንም ይሁን የዱንያ ማንኛውም ጉዳይ ሲገጥማቸው ሌላን አካል ሳያጋሩ ከእርሱ ብቻ ተስፋ ያደርጋሉ።

ዱዓ ሲያደርጉ ጠቃሚ እና ሁሉን ጠቅልሎ በያዘው ዱዓ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

"እነዚያም "ጌታችን ሆይ! ከሚስቶቻችንና ከዘሮቻችን ከዓይኖች መርጊያን ከእኛ ስጠን። አላህን ከሚፈሩትም መሪ አድርገን" የሚሉት ናቸው።"

ይህ ዱዓ በጣም ጠቅላይ የሆነና ጠቃሚ የሆነ ዱዓ ነው። ባሪያው አይኑ የሚያርፍበት ፣ ልቡ በመልካም ነገሮች የሚጎናጸፍበት ፤ ቤተሰቦቹ ፣ ልጆቹ በአምልኮታቸው ፣ ከወላጆቻቸው ጋር ባለው መልካም ግንኙነት ፣ በኑሯቸው ፣ በስነምግባራቸው እና በማንኛውም እንቅስቃሴያቸው የሚስተካከልበት ዱዓ ነው።

"አላህን ከሚፈሩትም መሪ አድርገን" በሚለው ዱዓ መልካም ባህሪን በመላበስና ነፍስን በማስተካከል ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ጌታቸውን የሚማጸኑበት ነው።

አንድ ባሪያ ከእርሱ በፊት የነበሩትን ደጋግ የአላህ ባሮችን እስካልተከተለ ፣ ከእሳት ድኖ ጀነት የሚወርስበትን መልካም ነገሮችን ለመላበስ እስካልተጋ ድረስ

የህብረተሰብ መሪ ሊሆን አይችልም። በዚህ አይነት ባህሪ ላይ ከሆነ አላህን የሚፈሩ ባሮች ሁሉ እርሱን ለመከተል ፣ የእርሱን አቅጣጫ ለመያዝ ይነሳሳሉ።

ስለዚህ እያንዳንዱ ቤተሰብ ትኩረት ሰጥቶ ዘወትር በዚህ ዱዓ ምላሱን ማለማመድ ይኖርበታል።

ማጠቃለያ

ይህን የተባረከ መልእክት ከዚህ በፊት ባሳለፍናቸው ውብ የሆኑ ስነምግባራት የተላበሱ ሰዎች በሚያገኙት ታላቅ ምንዳ ቁርኣኑን አሳረገ።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናገረ፡-

﴿أُوْلَئِكَ يُجْزَوْنَ الْغُرْفَةَ بِمَا صَبَرُوا وَيُلَقَّوْنَ فِيهَا تَحِيَّةً وَسَلَامًا﴾خَالِدِينَ فِيهَا حَسُنَتْ مُسْتَقَرًّا وَمُقَامًا﴾

"እነዚያ በመታገሳቸው የገነትን ሰገነቶች ይምመነዳሉ። በእርሷም ውስጥ ውዳሴንና ሰላምታን ይለሰላሉ። በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ሆነው (ይለሰላሉ)። መርጊያና መኖሪያይቱ አማረች።" (አልፉርቃን፡ 75-76)

ዋጋቸው በስራቸው አይነት ሆነ። ባህሪያቸው ከፍተኛ በመሆኑ ፣ በከፍተኛ የጀነት ክፍሎች ዋጋቸው መነዳቸው። በእርሱም ካሳቸው።

በጀነት የሚሰጣቸው ክፍል ምን እንደሚመስል ረሡል ﷺ በሚከተለው ሐዲሳቸው ገልጸውታል፡-

"إن أهل الجنة يتراءون أهل الغرف من فوقهم، كما يتراءون الكوكب الدري الغابر في الأفق، من المشرق أو المغرب، لتفاضل ما بينهم"

"በመካከላቸው ከመበላለጣቸው ልክ አብሪ ኮከቦች ከምስራቅ ወይም ከምአራብ አንደሚተያዩት የጀነት ሰዎችም ከበላያቸው ያሉትን የክፍል ባለቤቶች ይመለከታሉ።"

(ቡኻሪ፡ 3256)

የጀነት ሰዎች የክፍል ባለቤቶችን ለማየት ቅንጭላታቸውን ከፍ ያደርጋሉ። ልክ ከሰማይ ላይ ያሉ ከዋክብቶችን ከታች ሆነን እንደምንመለከተው ክፍሎቻቸውን ይመለከታሉ። ይህ የሚጠቁመው በጀነት ጸጋዎች ያላቸው ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑን ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

"በእርሷም ውስጥ ውዳሴንና ሰላምታን ይለዋወጣሉ።"

የጀነት ሰዎችን መላእክቶች ከጉድለት ፣ ከበሽታ ፣ ከቂም እና ከጥላቻ ነጻ መሆናቸውን በሚገልጸው ሰላምታ አቀባበል ያደርጉላቸዋል።

ይህ ነው የአላህን ኪታብ በትክክል የተከተሉ ፣ አላህን በአግባቡ የተገዙና ከእርሱ ዘንድ ልቅና ያላቸው ሰዎች ፍጻሜ።

አላህ በመጨረሻ አንቀጹን ሲያሟላ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿قُلْ مَا يَعْبَأُ بِكُمْ رَبِّي لَوْلَا دُعَاؤُكُمْ﴾

"ጸሎታችሁ ባልነበራት ኖሮ ጌታየ እናንተን ከምንም አይቆጥራችሁም ነበር።"

ይህ የቁርኣን አንቀጽ የመልካም መጎናጸፍና ከእሳት መውጫው አላህ ለእርሷ ብሎ እንዲሁም እርሷን ለማረጋገጥ ብሎ የፈጠረባት አምልኮት ፍጹም ለአላህ በማድረግ መሆኑን ይጠቁማል።

ኢብን አልቀይም ﵀ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"የዚህች አንቀጽ ትክክለኛው የሆነው ትርጉሟ፡ አላህ የፈጠራችሁ ለአምልኮ ብሎ ነው ስለዚህ አምልኮታችሁ ባትኖር ጌታየ በእናንተ ምን ይሰራል?" (ሚፍታሁ ዳሪ አስ'ሳዓዳ፡ 2/84)

የትክክለኛ ባሮቹን ባህሪያት የምናሟላ እንዲያደርገን ፤ በሐቅ ፣ ቀጥ ባለው ጎዳና እና በኢማን ላይ እንዲያጸናን አላህን እንማጸነዋለን። እኛንም በአጠቃላይ ሙስሊሞችንም ከንግግርም ይሁን ከተግባር እርሱ ለሚወደውና ለሚቀበለው እንዲመራን እንለምነዋለን። በአላህ እንጅ ሀይልም ብልሃትም የለንም።

الحمد لله رب العالمين، وصلى الله على نبينا محمد، وعلى آله وصحبه وسلم تسليما كثيرا دائما إلى يوم الدين



ባህር ዳር በሚገኙ የአህሉሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐደራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ኪንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq